# የብልጽግና ፓርቲ

## የኮር አመራር ምልመላ መመሪያ ቁጥር………/2016 ዓ.ም

## (ረቂቅ)

ሚያዚያ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ይዘት


መግቢያ ....... 1
**ክፍል አንድ ....... 2**
**ጠቅላላ ድንጋጌዎች ....... 2**
አንቀጽ አንድ- አጭር ርዕስ ....... 2
አንቀጽ ሁለት- ትርጓሜ ....... 2
አንቀጽ ሶስት- የጾታ አገላለጽ ....... 3
አንቀጽ አራት- የመመሪያው ዓላማ ....... 3
አንቀጽ አምስት- የኮር አመራር ምልመላ መርሆዎች ....... 3
አንቀጽ ስድስት- የኮር አመራር ልየታ ተፈፃሚነት ወሰን ....... 4
**ክፍል ሁለት ....... 4**
**የኮር አመራር ምልመላ ሂደት እና የምልመላ መስፈርት ....... 4**
አንቀፅ ሰባት- የኮር አመራር ምልመላ ሂደት ....... 4
አንቀጽ ስምንት- የኮር አመራር ምልመላ መስፈርት ....... 5
**ክፍል ሶስት ....... 8**
**ኮር አመራር ምልመላን ስለማደራጀት፤ ስለማጽደቅ እና ስለመከለስ ....... 8**
አንቀጽ ዘጠኝ- የኮር አመራር ምልመላ ስለማፅደቅ ....... 8
አንቀጽ አስር- የኮር አመራር ምልመላ መረጃን ማደራጀት ....... 8
አንቀጽ አስራ አንድ- የኮር አመራር መረጃን ስለመከለስ ....... 8
አንቀጽ አስራ ሁለት- ኮር አመራር ሆኖ ስለመቆየት ....... 8
**ክፍል አራት ....... 9**
**የፓርቲ ጽ/ቤቶች በኮር አመራር ምልመላ ሰራ ላይ ያላቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት ....... 9**
አንቀጽ አስራ ሶስት- ብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት ....... 9
አንቀጽ አስራ አራት- በየደረጃዉ የሚገኙ ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ....... 9
አንቀጽ አስራ አምስት- የተለዩ ኮር አመራሮች ስለመጠቀም ....... 10
**ክፍል አምስት ....... 11**
**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ....... 11**
አንቀጽ አስራ ስድስት- ከኮር አመራር ስለመታገድ ....... 11
አንቀጽ አስራ ሰባት- ቅሬታ ስለማቅረብ እና የማስተናገድ ሁኔታ ....... 11
አንቀጽ አስራ ስምንት- መመሪያውን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር ....... 11
አንቀጽ አስራ ዘጠኝ- መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ ....... 11

**መግቢያ**

*የብልፅግና ፓርቲ በአገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ራዕይን እውን ለማድረግ በአስተሳሰባቸው፣ በስነ ምግባራቸው፣ በእውቀታቸው፣ በክህሎታቸውና በአፈፃፀም ብቃታቸው የላቁ ኮር አመራሮችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማፍራት የሚያስችል ሥርዓት መፍጠር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣*

*በወሳኝ የፓርቲና መንግስት የሐለፊነት መደቦች ላይ ተመድበው ውጤት ማምጣት የሚችሉ እና የተለየ የአመራር ብቃት በሚጠይቁ ተልእኮዎች ላይ በመሰማራት የፓርቲው ተጨባጭ አቅም ሊሆኑ የሚችሉ አመራሮችን በመለየት አቅማቸውን መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ፣*

*በየደረጃው ባለው የመንግስት ተቋማት እና የፓርቲ ጽህፈት ቤቶች የሚገኝ የኮር አመራሮችን መረጃ በጥራት እና ወጥ በሆነ መንገድ አደራጅቶ በማስቀመጥ እና አመራሩ ቁልፍ ለሆኑ ተልዕኮዎች ለስምሪት ሲፈለግ መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ፤*

*የፓርቲያችንን ራዕይ፣ እሴቶች፣ አላማዎች እና ግቦች በአግባቡ የተገነዘቡ፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን የአመራር ብቃት የተላበሱ እና ለሌሎች አመራሮች ተሞክሮአቸውን ማካፈል የሚችሉ ኮር አመራሮችን መለየትና ለተልእኮ ዝግጁ ማድረግ በማስፈለጉ፣*

*ኮር አመራሮችን በጥራት ለማፍራት እና የኮር አመራር ስምሪታችን የፓርቲውን አሰራር ስርዓትን የተከተለ እንዲሆን የሚያግዝ በመሆኑ፣*

*በየደረጃው ካሉ አመራሮቻችን በንድፈ ሀሳብ የተሸሉ፣ የጠራ አመለካከት እና ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸው፤ ተጨባጭ ውጤት ያስመዘገቡ፤ በአባላትና ህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፤ በሚሰጡት አመራር ምሳሌ የሆኑ፤ አቅም፣ ብቃት እና ተነሳሽነት ያላቸው፤ በአመራር ምዘና ውጤት በጣም ከፍተኛ ዉጤት ያስመዘገቡ እና ግንባር ቀደም የሆኑትን ኮር አመራሮችን በመስፈርት መመልመል ጠንካራ ፓርቲ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ በመሆኑ፣*

*ተቋማዊ መሠረት ያለው ከማንኛውም አድሏዊ አሠራር ነፃ የሆነ ግልጽና ውጤታማ የኮር አመራር ምልመላ ሥርዓት መዘርጋት የለውጥ ቀጣይነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣*

*በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 40 መሰረት የኮር አመራር ምልመላ ለማካሄድ ያስችል ዘንድ ይህ የኮር አመራር ምልመላ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡*

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ አንድ- አጭር ርዕስ

*ይህ መመሪያ "**የብልጽግና ፓርቲ የኮር አመራር ምልመላ መመሪያ**" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።*

## አንቀጽ ሁለት- ትርጓሜ

1. **"አባል"** ማለት የብልፅግና ፓርቲን መተዳደሪያ ደንብ እና ፕሮግራምን ተቀብሎ የአባልነት መብትና ግዴታውን የሚወጣ የፓርቲዉ አባል ማለት ነዉ።
2. **"አመራር"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ አባል የሆኑ እና በፓርቲዉ አማካኝነት በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በየደረጃው ባለው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና በልዩ ልዩ የአመራርነት ቦታዎች በሹመት፣ በምደባ ወይም ሃላፊነት የተሰጣቸዉ የፓርቲዉ አባላት ናቸው።
3. **"ወረዳ"** ማለት በክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የወረዳ ደረጃ የተሰጣቸው የአስተዳደር አካላትን ያጠቃልላል፡፡
4. **"ዞን"** ማለት ለክልል ተጠሪ የሆኑ የዞን አስተዳደሮች፣ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች እና በዞን ደረጃ ያሉ ከተሞችን እና ልዩ ወረዳዎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡
5. **"ክልል"** ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፡፡
6. **"ኮር አመራር"** ማለት በየደረጃው ባሉ በመንግስት ተቋማት፣ የፓርቲ ጽህፈት ቤቶች እና በልዩ ልዩ የአመራርነት ቦታዎች በሹመት ወይም በምደባ በማገልገል ላይ ከሚገኙ አመራሮች የጠራ አመለካከት ያላቸው፣ ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸው፣ በተግባር አፈፃፀም ተጨባጭ ውጤት ያስመዘገቡ፣ በሚሰጡት አመራርነት ምሳሌ የሆኑ፣ አቅም፣ ብቃት እና ተነሳሽነት ያላቸው፣ በአመራር ምዘና ውጤት በጣም ከፍተኛ ዉጤት ያስመዘገቡ እና ግንባር ቀደም የሆኑ አመራሮች ማለት ነዉ።
7. **"አስተባባሪ ኮሚቴ"** ማለት የፓርቲና የመንግስት ሥራዎችን አቀናጅቶ በበላይነት የሚያስተባብር እና በፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተግባር ላይ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው አደረጃጀት ነው።

8. **“የፓርቲ አመራር ኮሚቴ”** ማለት በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እና በየደረጃው በብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓርቲ ስራዎችን አቀናጅቶ የሚመራ፣ የሚያስፈጽምና የሚፈጽም የአመራር ኮሚቴ ማለት ነው፡፡
9. **“የአመራር ምዘና ዉጤት”** ማለት አመራሩ በውስጠ ፓርቲ ስራዎች አፈፃፀም ምዘና እና በተመደበበት ተቋም መደበኛ ሥራዎች አፈፃፀም ምዘና በፓርቲዉ ምዘና መመሪያ መሠረት ያገኘዉ ውጤት ማለት ነው።
10. **“መርህ አልባ ግንኙነት”** ማለት አንድ አመራር የግል ጥቅም ለማግኘት ወይም ሌላውን ለመጥቀም ወይም ሌላ እኩይ ዓላማን ለማሳካት ሲል ከፓርቲ መርሆዎችና እሴቶች ውጭ በሆነና ሕዝብን፣ሀገርንና ፓርቲን በሚጎዳ መንገድ ከሌሎች አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች የሚያጠቃልል ነው፡፡
11. **“መልካም የፓርቲ ሥነ-ምግባር”** ማለት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተደነገጉ የአባልነት ግዴታ፣ የፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና አሰራሮችን ማክበርና በጥብቅ መፈፀም እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚስማማባቸውን የግብረ-ገብ እሴቶችን ማክበርና መልካም ተግባራትን በመፈጸም አርአያ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ ሶስት- የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጹት ሃሳቦች በሙሉ የሴት ፆታን የሚያመላክቱ ይሆናል።

## አንቀጽ አራት- የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ ግልፅ፣ አሳታፊና ወጥ የሆነ አሠራር በመዘርጋት ኮር አመራሮችን በጥራት በመመልመል እና በመገንባት የፓርቲን አመራር ማጠናከር ነዉ።

## አንቀጽ አምስት- የኮር አመራር ምልመላ መርሆዎች

የኮር አመራር ምልመላ በሚከተሉት መርሆዎች የሚመራ ይሆናል።

1. የኮር አመራር ምልመላ ስራ እውነተኛ መረጃ እና ማስረጃን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. የኮር አመራር ምልመላ ስራ አሳታፊ፣ አካታች፣ ከወገንተኝነት እና አድሎዓዊነት ነፃ የሆነ መሆን ይኖርበታል፡፡

3. የምልመላ ሂደቱ የሴቶች፤ ወጣቶች፣ ምሁራን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል።
4. የኮር አመራር ምልመላ በየደረጃው ሲከናወን በግልጽ አሰራርን የተከተለ መሆን ይኖርበታል። አሰራርን ያልተከተለ የኮር አመራሮች ልየታ ተጠያቂነትን ያስከትላል።
5. የኮር አመራር ምልመላ ስራ እውቀትን፣ ክህሎትን ፣ስነ-ምግባርን  እና የተግባር ውጤታማነትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።
6. የኮር አመራር ምልመላ ስራ ጥራቱን የጠበቀ፣ መፃኢ የፓርቲያችንን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ እና ለሚፈለገው ዓላማ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል።
7. የኮር አመራር ምልመላ ስራ በአመራር ስርዓታችን፣ በብቃት እና በህብረ-ብሔራዊነት መካከል ሚዛን ለማስጠበቅ የሚያስችል ሊሆን ይገባል።

**አንቀጽ ስድስት- የኮር አመራር ልየታ ተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በየደረጃው ባሉ የመንግስትና የፓርተ መዋቅራዊ አደረጃጀቶች ማለትም ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ በተለያዩ የአመራርነት እርከን ተመድበው ወይም ተሹመው በመስራት ላይ የሚገኙ የብልፅግና ፓርቲ አባል የሆኑ አመራሮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

## የኮር አመራር ምልመላ ሂደት እና የምልመላ መስፈርት

**አንቀፅ ሰባት- የኮር አመራር ምልመላ ሂደት**

1. በየደረጃዉ ባሉ አደረጃጀቶች በተልዕኮ እና በእቅድ አፈፃፀም ዉጤታማነታቸዉ፣ ለፓርቲያቸዉ ባላቸዉ እምነትና ቁርጠኝነትን መሰረት በማድረግ ኮር አመራሮች እንዲመለመሉ ይደረጋል፤
2. የኮር አመራር ምልመላ ስራ በአመት ሁለት ግዜ የአመራር ምዘናን ተከትሎ በለው አንድ ወር ውስጥ ይከናወናል፣
3. በእጩነት የተያዙት አመራሮች በዋና ጽ/ቤት በሚዘጋጀው ፈተና ተገቢውን ውጤት ማምጣት ይጠበቅባቸውል፣

4. በፈተናው ተገቢውን ውጤት ያስመዘገቡ እጩ የኮር አመራሮች ያለቸው ስነ-ምግባር እንዲጣራ ይደረጋል፣
5. የስነምግባር ማጣራት ሂደቱን ያለፉ እጩ ኮር አመራሮች መረጃቸው ተደራጅቶ እንዲጸድቅ ይደረጋል፡፡
6. ለኮር አመራርነት የሚመለመሉ አመራሮች የተቀመጠውን የምልመላ መስፈርቱን ሙሉ በሙሉ የሚመለመሉ መሆን አለባቸው፡፡
7. ለኮር አመራር የሚቀርቡ /የሚወዳደሩ/ አመራሮች በምልመላ ወቅት የምዘና ውጤታቸው በተከታታይ ለሁለት ጊዜ በጣም ከፍተኛ የሆኑ አመራሮች ብቻ ነቸው፡
8. የተቀመጠውን መስፈርት መሰረት በማድረግ ለኮር አመራር ብቁ ሆነው ከወረዳ፣ ከተማ እና ከዞን አመራር ፑል የተመለመሉ የአመራሮች መረጃ በክልል/ከተማ አስተዳደር/ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲጸድቅ ይደረጋል።
9. ከፌደራል እና ከክልል የአመራር መዋቅር ውሰጥ የኮር አመራር ምልመላ መስፈርቱን አሟልተው የተመለመሉ አመራሮች መረጃ በፓርቲ በዋና ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ እንዲጸድቅ ይደረጋል።
10. የጸደቁ ኮር አመራሮች መረጃ በክልል/ ከተማ አስተዳደር/ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና ዋና ጽሕፈት ቤት መረጃ ቋት ውስጥ እንዲደራጁ ይደረጋል።

## አንቀጽ ስምንት- የኮር አመራር ምልመላ መስፈርት

ኮር አመራር ሆኖ የሚመለመል አመራር ቀጥሎ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት።

1. **የአፈፃፀም ብቃት** (70%)

   ሀ) ኮር አመራር ሆኖ የሚመለመል አመራር በሁለት ተከታታይ የአመራር ምዘና ውጤቱ በጣም ከፍተኛ ውጤት ያገኘ መሆን አለበት፣

   ለ) የሚመራውን ተቋም ዕቅድ፣ ከፓርቲ እና መንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የ10 አመት መሪ እቅዶች ጋር አጣጥሞ ማቀድና መከወን የሚችል፣

   ሐ) የእቅድ አፈፃፀሙን በተከታታይ የሚገመግም፣ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግና ግብረ መልስ የሚሰጥ፣

   መ) በተቋሙ በዕቅድ የተያዙ ተግባራት በአፈፃፀም የላቀ ውጤት ያስመዘገበ፣

   ሠ) የተሰጠውን ተልዕኮ በተነሳሽነት፣ በቁርጠኝነት እና በውጤታማነት የሚተገብር እና ለተግባራዊነቱ የሚተጋ፣

ረ) ስራውን አሳታፊና ሃይል በሚያሰባስብና በተደራጀ አግባብ የሚፈፅም፣

ሰ) በየጊዜው በአዳዲስ ውጤት የታጀበና ተጨማሪ አቅም እየፈጠረ የሚሄድ፣

ሸ) ለፈተናዎች የማይንበረከክ፣ የዓላማ ፅናት ያለው፣ የተልዕኮ አፈፃፀም ሳንካዎችን ማሸነፍ የሚችል እና ፈተናን ወደ ዕድል የመቀየር ተሰጥኦን ተጎናፀፈ፣

2. **ጠንካራ እውቀትና ክህሎት ያለው** (30%)

ሀ) በፓርቲው መሰረታዊ እሳቤዎች፣ አስተምህሮዎች እና መመሪያዎች ላይ ኮር አመራሮችን ለመለየት በማዕከል ተዘጋጅቶ የሚሰጠውን ፈተና ከ25 እና ከዛ በላይ ነጥብ በማምጣት ያለፈ፣

ለ) በብልፅግና ፓርቲ በመደመር እሳቤ፣ በፓርቲ ፕሮግራም፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ መተዳደሪያ ደንብ እና መመሪያዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ያለው እና ከልቡ ያመነበት፣

3. **ስነ-ምግባር (ማለፍ/መውደቅ)**

ሀ) ከሌብነት እና ከብልሹ አሰራር የፀዳ፤

ለ) የሚመራው ተቋም ከሌብነት እና ከብልሹ አሰራር እንዲፀዳ የሚያደርግ፤

ሐ) የፓርቲውንና መንግስት ሚስጥርን የሚጠብቅ፤

መ) ፓርቲው የሚሰጠውን ተልዕኮ በእምነት ተቀብሎ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ የሚያደርግ፤

ሠ) የውሸት ሪፖርትን የማያስተላልፍ እና ለትክክለኛነቱ የሚተጋና የሚታገል፤

ረ) የተቋሙን አሰራር ስርዓት በጠንካራ ዲሲፕሊን የሚተገብር እና እንዲተገበሩ ብቃት ያለው አመራር የሚሰጥ፤

ሰ) የተቋሙን ሀብት እና ንብረት ለታለመለት ዓላማ ብቻ የሚያውል እና እንዲውል የሚያደርግ፤

ሸ) ከላይ የተገለፁ (ከ "ሀ-ሰ") ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ፓርቲው ሌሎች ለዚህ ምዘና አጋዥ የሆኑ ተቋማትን ለመጠቀም በሚስጥራዊነት አመራሩ ያለውን ስነ-ምግባር ያጣራል፡፡

4. **በኮር አመራርነት ስለመያዝ**

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለፁ መስፈርቶች (የአፈፃፀም ብቃት፣ እውቀት እና ክህሎት) ውጤት ተደምሮ አመራሩ የሚያገኘው ውጤት 95 እና ከዚያ በላይ ከሆነ በኮር አመራርነት ይያዛል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "ሀ" ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 3 የተመላከተው የስነ-ምግባር መስፈርትን ያላሟላ አመራር ወይም በስነ-ምግባር ውጤት የወደቀ አመራር በኮር አመራርነት አይያዝም፡፡

5. **በአመራር ምዘና ያገኘው ውጤት**

ከላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ለአመራር ምዘና ማስፈጸሚያ በተዘጋጀው መመሪያ ቁጥር 10/2015 መሠረት በሚካሄደው የአመራር ምዘና አጠቃላይ ውጤቱ በሁለት ተከታታይ ምዘናዎች በጣም ከፍተኛ ውጤት ያገኘ አመራር መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

6. **ሌሎች የፓርቲ ግዴታዎች**

ሀ) የአባልነትና የአመራር ግዴታውን ለመወጣት የግሉን እና የቡድኑን ዕቅድ በብቃት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደረገ፤

ለ) የአባልነት መዋጮን ጊዜውን ጠብቆ የሚከፍል እና ሌሎች እንዲከፍሉ የሚያደርግ፤

ሐ) በወረዳ አደረጃጀት፣ ህዋስ እና የመሰረታዊ ድርጅት ስብሰባዎች የሚሳተፍ እና ለአደረጃጀቱ መጠናከር የጎላ አስተዋጽኦ የሚያበረክት፤

መ) የፓርቲውን የውስጥ አሰራር ከሚጎዱ እሳቤዎች እና ድርጊቶች የፀዳ፤

ሠ) ለፓርቲው እና ለሚመራው ተቋም ግብዓት የሚሆኑ አስተሳሰቦችን አደራጅቶ የሚያቀርብ፤

ረ) የፓርቲውን ማህበራዊ መሰረት ለማስፋት በተግባራቸዉ ዉጤታማ የሆኑ አዳዲስ አባላትን የሚያፈራ፤

ሰ) በተመደበበት ተቋም የአባላት እና አመራርን አንድነት፣ ነፃነት እና ቁርጠኝነት ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ተከታታይ ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግ፤

# ክፍል ሶስት

# ኮር አመራር ምልመላን ስለማደራጀት፤ ስለማጽደቅ እና ስለመከለስ

## አንቀጽ ዘጠኝ- የኮር አመራር ምልመላ ስለማፅደቅ

1. በወረዳና ዞን ደረጃ የተመለመሉ ኮር አመራሮች መረጃ በክልል ፓርቲ አመራር ኮሚቴ ተደራጅቶ በክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚጸድቅ ይሆናል።
2. በክልልና ፌዴራል ደረጃ የተመለመሉ ኮር አመራሮች መረጃ በዋና ጽ/ቤት ፓርቲ አመራር ኮሚቴ ታይቶ የሚጸድቅ ይሆናል።

## አንቀጽ አስር- የኮር አመራር ምልመላ መረጃን ማደራጀት

በየደረጃዉ የተመለመሉ ኮር አመራሮች መረጃቸዉ በክልል ፓርቲ በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና በፓርቲዉ ዋና ጽህፈት ቤት የአመራር መረጃ ቋት ዉስጥ የሚደራጅ ይሆናል።

## አንቀጽ አስራ አንድ- የኮር አመራር መረጃን ስለመከለስ

1. በየደረጃው የተደራጀው የኮር አመራር መረጃ ተደራሽ፤ ወቅታዊ እና ተአማኒ እንዲሆን በዓመት ሁለት ጊዜ መከለስ ይኖርበታል።
2. በኮር አመራርነት የተመለመለ አመራር በተከታታይ ምዘና ውጤት ኮር ሆኖ መቀጠል ካልቻለ ከኮር አመራርነት ሊወርድ፣ ከምልመላ ቋትም ሊወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት- ኮር አመራር ሆኖ ስለመቆየት

ኮር አመራር ከተመለመለበት ጊዜ ጀምሮ በሚሰጠዉ ተዕልኮ ውጤታማነት፣ በዚህ መመሪያ በተቀመጡ መሰፈርቶችን በሙሉ ማሟለቱ በመቻሉ እና በየስድስት ወሩ በሚደረግ የአመራር ምዘና በሚያስመዘግባቸዉ ውጤት የሚወሰን ይሆናል።

# ክፍል አራት

# የፓርቲ ጽ/ቤቶች በኮር አመራር ምልመላ ስራ ላይ ያላቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት

## አንቀጽ አስራ ሶስት- ብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. የክልልና የፌዴራል ኮር አመራር ሂደት በማደራጀት እንዲጸድቅ ያደርጋል፤
2. በክልልና ፌዴራል ደረጃ የተለዩ ኮር አመራችን በተመለከተ በየግዜው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
3. በየግዜው ምዘናን ተከትሎ ለእጩ ኮርነት ለተመለመሉ አመራሮች የሚመጥን የብቃት ምዘናን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ በማድረግ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
4. በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ፣ ከነባሩ የመረጃ ቋት ጋር የተቀናጀ ኮር የአመራር መረጃ ቋት ማልማት፤
5. ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በኮር አመራር ምልመላ ዓላማ፣ አፈጻጸም ሂደት ላይ ስልጠና መስጠት፤
6. ለክልሎች እና ለከተማ አስተዳዳሮች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች አመራርና ባለሙያዎች የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና መስጠት እና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በቴክኖሎጂ ግብአት ማበልፀግ፤
7. ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ እና ግብረ መልስ መስጠት፤
8. በኮር አመራርነት የተመለመሉ አመራሮችን የማስፈፀም አቅማቸው እና ብቃታቸው የማሳደግ ሥራ ይሠራል።
9. ከክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የሚላከዉን መረጃ ማጣራት፤ በአግባቡ ማደራጀት፤ ማስተዳደርና ለታለመለት ዓላማ መጠቀም፤

## አንቀጽ አስራ አራት- በየደረጃዉ የሚገኙ ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. በየደረጃዉ ለሚገኙ ፓርቲ አመራሮች ኮር አመራር ምልመላ ዓላማ፣ አፈጻጸም ሂደት ላይ በየጊዜዉ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፤

2. ከክልሉ የፓርቲና የመንግስት መዋቅር የተመለመሉ ኮር አመራሮች ምልመላን በመስፈርቱ መሰረት ያካሂዳል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ትክለኛነቱን ያረጋግጣል፤ ለክልል አስተባባር ኮሚቴ በማቅረብ ያጸድቃል።
3. የኮር አመራር ምልመላ በተቀመጠዉ የጊዜ ሠሌዳ እንዲካሄድ ያደርጋሉ።
4. የተመለመሉ ኮር አመራሮችን በኮር አመራር ቋት ውስጥ ያደራጃሉ፤ ለዋና ጽ/ቤት በሪፖርት ያሳዉቃል፤
5. የተመለመሉ ኮር አመራሮችን ተልዕኮ ሰጥቶ ያሰማራል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ ይገመግማል፤ ይመዝናል፤
6. በኮር አመራርነት የተመለመሉ አመራሮችን የማስፈፀም አቅማቸው እና ብቃታቸው የማሳደግ ሥራ ይሠራል።

## አንቀጽ አስራ አምስት- የተለዩ ኮር አመራሮች ስለመጠቀም

1. የተመለመለውን ኮር አመራር በሁሉም እርከን ፓርቲ ያለውን የሰው ሃይል አቅምና ተነሳሽነት አውቆ ለተልዕኮ ዝግጁ ለማድረግ ይጠቀምበታል፡፡
2. በምዘና፣ በተግባር አፈጻጸም፣ በስነ-ምግባር እንዲሁም በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ የአመራር ጉድለት ሲያጋጥም በጥንቃቄ አመራር ለመተካት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
3. ከአሰራር ውጭ በተለምዶ አመራር የመተካት ሂደቶች እንዲቀሩ እና ፓርቲው የጠንካራ አመራር ስብስብ እንዲሆን በማድረግ ውጤታማነቱን ለማሳደግ ያግዛል፡፡
4. አመራር በሚተካበት ጊዜ በኮር አመራር ልየታ ቅደም ተከተል መሆን አለበት፡፡
5. ኮር አመራር የመመልመል ሂደት በአመራር ቋት ከተያዙት መካከል በአመራር ምደባ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት በየደረጃው ባለው አስተባባሪ ኮሚቴ ታይቶ አንድ ደረጃ ከፍ ባለው አስተባባሪ ኮሚቴ እየተወሰነ የሚተካ ይሆናል፡፡
6. በኮር አመራር ፑል ካልተያዘ በስተቀር ወይም በልዩ ሁኔታ ከሙያ ጋር ተያይዞ የሚሾም ወይም የሚመደብ አመራር ካልሆነ በስተቀር ከኮር አመራር ቋት ውጭ በተለምዶ መመደብ ክልክል ነው፡፡
7. በተለያዩ ምክንያቶች የኮር አመራር በሚያስፈልግበት ወቅት በኮር አመራርነት የተመለመሉ ሴት እና ወጣት አመራሮች ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ አስራ ስድስት- ከኮር አመራር ስለመታገድ

1. በአፈፃፀም ድክመት፤ በዲሲፕሊን ግድፈት፤ በብልሹ አሰራር እና በሰርጎ ገብነት የተገመገመ አመራር ከኮር አመራር ቋት የሚታገድ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ አንድ ኮር አመራር በራሱ ፍቃድ ከኮር አመራር ቋት ሊወጣ ይችላል።
3. ኮር አመራሮች ለኮር አመራርነት ያበቃቸውን መስፈርቶች በቀጣይነት ሳይፈጽሙ ሲቀር፣ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ እሴቶች፣ መርሆዎች የሚጥሱ እና የዲሲፕሊን ግድፈት ፈጽመዉ መገኘታቸው በየደረጃው ባሉ አደረጃጀቶች ከተረጋገጠ ከኮር አመራርነት የሚሰረዝ ይሆናል።

## አንቀጽ አስራ ሰባት- ቅሬታ ስለማቅረብ እና የማስተናገድ ሁኔታ

በየደረጃው በሚካሄደው የኮር አመራር ምልመላ ላይ ቅሬታ ያላቸው አመራሮች በብልጽግና ፓርቲ የአመራርና የአባላት የዲሲፕሊን መመሪያ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት መሰረት ቅሬታቸውን በማቅረብ መስተናገድ ይችላሉ።

## አንቀጽ አስራ ስምንት- መመሪያውን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር

ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሊያሻሽለው ወይም ሊቀይረው ይችላል።

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ- መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ ከጸደቀበት ከ………….. ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

**ዐብይ አህመድ(ዶ/ር)**

**የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት**

**ሚያዝያ 2016 ዓ.ም**